M06/1/A1AMH/HP1/AMH/TZ0/XX
22060013

**AMHARIC A1 – HIGHER LEVEL – PAPER 1**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU SUPÉRIEUR – ÉPREUVE 1**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL SUPERIOR – PRUEBA 1**

Monday 22 May 2006 (morning)
Lundi 22 mai 2006 (matin)
Lunes 22 de mayo de 2006 (mañana)

2 hours / 2 heures / 2 horas

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a commentary on one passage only.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Rédigez un commentaire sur un seul des passages.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario sobre un solo fragmento.

**1.** (ለ)

# የማን ምን ነው

አዳም እንጂ ሄዋን እንጂ
ቅንጦት ኑሮ ቢያስጠላቸው
ከሰላሙ ከገነት ቤት
ቅንጣት ፍሬ ከዛፉ መዘው
ካምላክ ስልጣን ወንበር ወርሰው
ሊሾሙበት ሊሸሩበት
እንዲላላክ እሱን ሊያዙት
እነርሱ እንጂ ባምሮታቸው
ስልጣን ሽተው የቀመሱት
እኛ ታዲያ በማን ዳፋ
አንዴ ከላይ አንዴ ከታች
ከምድር ጋር እንገፋ
አርሰን አጭደን ለከርሳችን
እንደሰት እንከፋ
እንፋቀር እንጣላ
ብንጣላስ ባንስማማ
ባንፋቀር ብንባላ
እንደ አዳም እንደ ሄዋን
እንደነርሱ ማን ነው የሰራ?
ከሱ በላይ ስልጣን ሽቶ
የበለስን ፍሬ የበላ::
አልቀመስንም የት አግኝተን
አልደላንም መች ቁጭ ብለን
ጌታን ልንዋሽ መና በልተን
ጥረን ግረን ለምን በላው
ብለን እንጂ ለከርሳችን
እንደነርሱ ቁጭ ብለን
መና ቢሆን ምግባችን
ማናችን ነን ከማን ጋራ
ምን ጉዳይ ነው የሚያጋጨን?::
አምላክ እንጂ ልፉ ብሎ
ጣሩ ብሎ

ባዳም ስተት እኛን ቀቶ
ስንገፋ ስንገፋ ሆዳችንን እንድንሞላ
መኖር አንችል ካልተበላ
ደሞሞ ሲጎድል ስናጣ ነው
እርስ በእርስ ምንባላ
በሀሰት ቃል ም' ን መስክር
በሰንበት ቀን ም' ንሰራ
እንዲም ሆኖ ለተኖረው
ምድር መኖር ጥቅም ካጣ
ሰማይ ቤትን ለማሳመር
ከሆነማ ም'ንደክመው
የምንዘራው የምናጭደው
የምን ሰማይ የምን ምድር
የም'ን ምን ነው ሰላም ያለው?፡፡
ገነትንም በነአዳም አይተነዋል
ምድርንም በኛው ህይወት ኖረነዋል
ምኞት አምሮት እዛም ካለ
ከምድሩ ካልተለየ
የማን ምን ነው ሰላም ያለው
የማይደክም የማይርበው
የማን ምን ነው? የምን ምን ነው?
ለአምላክ ብሎ የሚኖረው?፡፡

ትርሲት በቀለ፣ ፍላጻ ፣ሳምኬት ማተሚያ ቤት፣ **1997**፡፡